**ዶ/ር ሰይፉ ትርፌ**
**በኢትዮጵያ የአይ.አ.ሲ.ሲ ተወካይ**

# አዛርባጃን - ሁለተኛዋ አገሬ

**"ያኔ በእርስ በርስ ጦርነት እየታመሰች የነበረችውን አገሬን ኢትዮጵያን ለቅቄ ለመሄድ ስወስን ዋና አለማዬ የነበረው ትምህርትን ጨርሼ በምወደው የኢንጂነሪንግ ሞያ ሰልጥኜ አገሬን በተግባር ማገልገል ነበር፡፡ እውነታው ግን ይህ አልነበረም። ከአገሬ ስወጣ ሰሚን እንኳን የማላውቀው አገር ከትምህርቴ በተጨማሪ ትዳሬን፣ ሁለት ልጆቼን ፣ የዶክትሬት ዲግሬዬን ጥሩ የሚባል ስራና ከትውልድ ሀገሬ የማይተናነስ ፍቅርና መተሳሰር ሰጥታ አኖረችኝ፡፡"**

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ውጪ ሀገር የሄድኩበት ጉዞ ወደ ቀድሞው ሶቬት ህብረት ዋና ከተማ ሞስኮ ነበር። ይህም በዚያን ጊዜ ባገኘሁት የነፃ ትምህርት ዕድል አማካኝነት ሲሆን ጊዜውም እ.ኤ.አ በኦገስት 1989 ዓ.ም ነበር፡፡ በውቧ ሞስኮ ከተማ የ3 ቀን ቆይታ በኋላ ወደ ተመደብኩበት ወደ አዛርባጃን ሶቪየት ሪፐብሊክ ዋና ከተማ ባኩ ጉዞ በባቡር ጀመርኩ፡፡ እግዚአብሔር ባዘጋጀው አጋጣሚ የአሁኗ ባለቤቴ ወ/ሮ በላይነሽን ከሌላ አገር ምደባዋን ቀይራ ወደባኩ በምጓጓዝበት ባቡር ጣቢያ ለመጀመሪያ ጊዜ ተገናኘን። ከሁለት ቀን ተኩል የባቡር ጉዞ በኋላ ከአዛርባጃን ዋና ከተማ ባኩ አደረሰን፡፡

የመጀመሪያ ግንዛቤዬ ባኩ ተወልጄ የደግኩባትን የሀረር ከተማ፤ በተለይ አሮጌው ከተማ የሚባለው አካባቢ በግንብ የታጠረና ልክ አንድ ጀጐል ግንብ የተወሰኑ በሮች ሲኖሩት











የውስጥ መንገዶችም በጣም ጠባብ ናቸው። እያደር እንደገባኝ ግን ባኩ የፋርስ፤ የአውሮፓ እንዲሁም የሶቪየት ህብረት የከተማ ምህንድስና ጥበብ የሚስተዋልበት ከተማ ሆና አገኘኋት።

በከተማዋ በወቅቱ ብዙ ኢትዮጵያውያንና የተለያዩ አገራት ዜጎች ትምህርታቸውን ይከታሉ ነበር፡፡ የቋንቋ ትምህርታችንን ስንከታተል በነበረበት ጊዜ የምንኖርበት ካምፓስ መላውን ዓለም ይወክላል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ከተለያዩ የአፍሪካ ሃገራት አንስቶ እስከ አረብ ሀገራት፤ ኢስያ፤ ላቲን አሜሪካ ኧረ ስንቱ፡፡ ከየአቅጣጫው የሚንቆረቆረው የተለያዩ አገራት ሙዚቃ፤ በተለይ በበዓል ቀናት፤ የተለየ ስሜትን ይቀሰቅሳሉ ድምቀት ይሰጣሉ፡፡

ከእ.ኤ.አ 1991 ከሶቬት ህብረት መፈራረስ በኋላም አዛርባጃን በሯን በበለጠ ለዓለም ከፍታ "ኑ አብረን እንስራ" ብላ በጋበዘችበት ወቅት ከመላው ዓለም የጐረፉት ባለ ሃብቶች በተለይ ባኩን ዓለም አቀፋዊ ገጽታ አላብሰዋታል፡፡ እንግዳ ተቀባይና ሩሩህ ህዝቧ በፍጥነት ያላምዳል፡፡

ከሞስኮ ወደ ባኩ ባደረግነው የባቡር ጉዞ መተዋወቅና መግባባት የተጀመረው የኔና የበላይነሽ ግኑኘነት በዓመቱ በባኩ ከተማበትዳርሌላምእራፍያዘ፡፡ምንምእንኳንየሶቬትህብረትን መፈራስ ተከትሎ በተፈጠረ የኢኮኖሚ ቀውስ የፖለቲካ አለመረጋጋት እንዲሁም የተባበሩት መንግስት በተደጋጋሚ ያወገዘው የጐረቤት አገሯ አርሜኒያ የፈጸመችው ወረራና ያስከተለው ስደትና የመሳሰሉት ተድጋሮቶች ቢያጋጥሙንም ብዙዎቹ ኢትዮጵያዊያን የመጣንበትን ትምህርት በትእግስት ተከታትለን አጠናቀናል። ለዚህም መምህራኖቻችን የክፍል ጓደኞቻችን እንዲሁም ኢትዮጵያውያን ያደረግነው እርስ በርስ መረዳዳትና መደጋገፍ እጅጉን ጠቅሞናል፡፡

እኔም ትምህርቴን እ.ኤ.አ 1995 አጠናቅቄ በከፍተኛ ማእረግ ከተመረቅኩ በኋላ (ባለቤቴ በላይነሽም በዚሁ አመት ተመርቃለች) በአንድ ስደተኞችን በመርዳት ላይ በሚገኝ ወርልድ ቪዥን በሚባል ዓለም አቀፍ ግብረሰናይ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሬ ስራ ጀመርኩ ፡፡ ይህ አጋጣሚ አዛርባጃንን በይበልጥ እንዳውቃት፤ ልዩ እሴቶቿን በጥልቀት እንድመረምርና እንድረዳ በር ከፈተልኝ። በስራ አጋጣሚ በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች ስዘዋወር በዛች ትንሽ አገር (አዛርባጃን በስፋት ከትግራይ ክልል ተመጣጣኝ ነች) ያለውን መልክዓ ምድርና የባህል ብዝሃነት በጣም የሚስብ ሆኖ





አግኝቼዋለሁ፡፡እንደ ትሮፒካል አካባቢ ብርትኳን፤ ሎሚና ሻይ ቅጠል ከሚበቅሉበት ሊንካራን አካባቢ፤ አብዛኛውን የዓመቱ ወራት በበረዶ ተሸፍኖ የሚቆዩት የባዛርዱዙና ሻህዳግ ተራሮች የኩራን ወንዝን ተከትሎ የሚገኘው ዝቅተኛና በረሃ ቀመስ አካባቢ ፣ በደን የተሸፈነ የታላቁ የካውካዝ የተራራ ስንሰለት ብቻ ባጭሩ ትንሿ አዛርባጃን በዓለም ላይ ያሉ የመልክአ-ምድርና የአየር ፀባይ በሙሉ አሉባት ቢባል ማጋነን አይሆንም። አዛርባጃናዊያንም ይህንን በኩራት ይገልፃሉ፡፡

የቤተሰባችን ይበልጥ አስደሳችና ልዩ ምዕራፍ የተከፈተው ሁለቱን ልጆቻችን ቤቲንና ሜሪን ወልደን በስራ ምክንያት ከባኩ ከተማ ተዛውረን ሚንገቻቪር በሚባል ከተማ መኖር ስንጀምር ነበር። በስራና ሽርሽር ምክንያት ብዙ የአዛርባጃን የገጠር ከተሞችንና መንደሮችን ለመጎብኘት ችለናል። የነዋሪዎቹ ደግነታችንውና ቸርነታቸው መለኪያና ወደር የሌላቸው እሴቶችን በቅረቡ ለመተዋወቅ የረዳንም እንደዚህ በየጊዜው በምናደርገው ጉብኝት ውቅት ነበር፡፡ የጉባ ውብ የስጋጃ ምንጣፎች የ ላግች የመዳብና የነሀስ ግሩም ጌጣጌጦች የ ሼኪ ባቅላባና የሐር ስራ፤ የጐይቻይ የሩማን ፌሬና ጭማቂ ፣ የ ጋቡስታን ክፍት ጥንታዊ ሙዚየም፤ ልዩ የሆኑ የጭቃ እሳተ ገሞራዎች (በእሳት ምትክ ቀዝቃዛ ጭቃ የሚተፉ ቮልካኖዎት) ባኩ አካባቢ ያለው የማይጠፋው የተፈጥሮ እሳት (ያናር ዳግ) የ አታሸጋህ የ ጥንት የእሳት የአምልኮ ቦታ ኸረ ስንቱ ተዘርዝሮ ያልቃል፡፡ በነገራችን ላይ አዛርባጃን ዘጠኝ የማይዳሰሱና ሁለት የሚዳሰሱ ቅርሶች በ ዩኔስኮ ያስመዘገበች አገር ነች።

በጣም ከማይረሱን ነገሮች መካከል የእለት ተለይ ገበያ ስፍራ (ባዛር) ነው ፡፡ ከዓመት እስከ ዓመት በተለያየ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች፤ የእንስንሳትና የእርሻ ውጤቶች አይንን በሚማርክ ሁኔታ ተደርድረው ይሸጣሉ፡፡ ባዛር ሱስ የሚሆን ነገር ነው፡፡ ከሻጮቹ ጋር የሚደረግ የዋጋ ክርክር፤ እኛ በአፍሪካዊነታችን የሚደረግልን ጥሩ የዋጋ አስታየት፣ እንዲያውም በአንዳንድ ባዘር በነፃ ውሰዱ-አንወስድም እየተባባልን የምንገባበዘው መቼም አይረሳም፡፡

በበጋው ጊዜ ሙቀትን ለመሸሽ ከነቤተሰባችን ወደተዋቡና ጥቅጥቅ ወዳሉ ደኖች በመሄድ ግርጌ ድንኳን ጥለን እንዝናናለን። የአካባቢው ገበሬዎች እንኳን ደህና መጣችሁ ይሉን ነበር፤ በክፉት የሚያይ ማንም ሰው አልነበረም፡፡ ብቻችንን እልም ካለው ጫካና ዱር ውስጥ ስንውልና ስናድር አንዳችም ስጋት አድሮብን አያውቅም። ልዩ ከሆኑት የ *ዛካታላ፤ አጉዝ፤ ጋህ፤ ጋባላ፤ ሼኪ፤ ሻማኽ፤ ቶዥዝ፤ ጉሳር፤ ሃችማዝ፤ ማሳል፤ ሌንካራን፤ ጊያንጃ፤ ጌዴቤክ፤ ኢስማኢሊ* እና ከመሳሰሉት የተፈጥሮ መዝናኛ ቦታዎች ያሳለፍናቸው ጊዝያት በቤተሰባችን ትውስታ ለዘላለም ተጽፎ ይኖራል። በዚያ ስንሰማቸው የነበሩት ብርቅ የሙጋም ሙዚቃ ልባችንን ያስሸፍት ነበር። ሙጋም ከ አገራችን የትዝታ ዘፈን ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በ ዓለም ቅርስነት ተመዝግቧል።

የአዛርባጃን ሌላው ውለታ፤ በማስትሬት ዲግሪ በ 1995 ከተመረቅኩ ከአመታት በሁዋላ የ ፒኤችዲ ዲግሪ ምርምሬን በነጻ (ስኮላርሺፕ) እንድቀጥል እድል ተሰጥቶኝ፤ እ.ኤ.አ. በ 2005 ዓ.ም. በኢንጂነሪንግ በፒኤችዲ ዲግሪ ልመረቅ ችያለሁ። የስራ ሀላፊነቴም እያደገ መጥቶ የምሰራበትን ድርጅት በ ካንትሪ ዳሬክተርነት ለ 6 አመታት እ.ኤ.አ. እስከ 2010 ዓ.ም. አገልጌያለሁ። ባለቤቴ በላይነሽም ልጆቻችን በሚማሩበት በ "ባኩ ኢንተርናሽናል ስኩል" በ ሂሳብና እቃ ግዢ ስራ ለ 6 አመታት አገልግላለች።

ልጆቻችን እያደጉ ሲመጡ ጠበቅ ያለ የማንነት ጥያቄ ማንሳት ጀመሩ። ምንም እንኩዋን በ አዛርባጃን ተወልደው ቢያድጉም፤ የወላጆቻቸውን አገር በበለጠ ለማወቅ ጓጉ። በተለይ የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው በየጊዜው ወደ ትውልድ አገራቸው እየሄዱ ሲቀሩ፤ "እኛስ መቼ ነው ወደ ኢትዮጵያ እምንገባው" እያሉ በተደጋጋሚ መጠየቅ ጀመሩ። ይህንን ተከትሎ ከ ሀያ አንድ አመታት ቆይታ በኋላ ሁለተኛ አገራችን የሆነችውን አዛርባጃንን ለቅቀን በ እ.ኤ.አ. ጁላይ 2010 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ተመለስን። ከዚያ በፊት በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ ስንመላለስ ስለነበር ከመነሻው ኑሮ በ ኢትዮጵያ ብዙም አልከበደንም ነበር። እያደር ግን የአዛርባጃን ትዝታ እያደር በረታ። በተለይ የማይሰለቹትና ተወዳጅ ምግቦች፤ እንደ *ታንዲር ቾሬክ፡ ዛቮድ ቾሬክ፤ ላቫሽ፤ ካባብ (ሉላ፤ ትካ፤ባስቱርማ)፤ ፒቲ፤ ፕሎቭ፤ ጉታብ፤ ላቫንጊ፤*













ዶልማ፤ ዱሽባራ፡፤ ኩፍታ፤ ከዲዘርት ባቅላቫ፤ ሼኬርቡራ ና የመሳሰሉተን ስናስታውስ በደስታ እንሞላለን። የተቻለንን ያህል እነዚህን ምግቦች እዚሁ ለማዘጋጀት ሞክረናል፤ ብዙም ባይሳካም። በተለይ የ “ኑቭሩዝ ባይራም” በአል አከባበር ድምቀቱ ችቦው፤ ወቅቱ የህዝቡ ስሜት ከኛ አዲስ አመት ጋር ተመሳሳይነት ስላለው ትዝታው መቼም አይጠፋም።

አዛርባጃን እያለን ተዋወቅናቸው ከነበሩት ጓደኞቻችን ውስጥ ሁለት ቤተሰቦች በተለያየ ጊዜ እዚህ ኢትዮጵያ ድረስ መጥተው ጠይቀውናል። እኛም አንድ ቀን ሁለተኛ አገራችን የሆነችውን አዛርባጃንን ተመልሰን ሄድን ለመጎብኘት ብርቱ ፍላጎት አለን። ይውም ከእግዚአብሄር ፈቃድጋር እንደሚሳካ እናምናለን።

ይህን አጋጣሚ በመጠቅም አዛርባጃንን እንደ ሁለተኛ አገሬ እንድቆጥራት ያደረገኝን፤ ከሚገባኝ በላይ ተከብሬ እንድኖር ያስቻለኝን ሰፊውን የአዘርባኢጃን ሕዝብ ላመሰግን እወዳለሁ።